እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድኩት፤
ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት፤
ት.ሆሴዕ ፲፩፥፩

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፫ ርእሰ አንቀጽ
፬ ሪፖርታዥ
፮ ቤተ አብርሃም
፲ ቃለ መጠይቅ
፲፯ የሕፃናት ዓምድ
፲፰ ትዝብት
፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ


## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ


ጳጉሜን ፩ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
Simatsidk12@gmail.com

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ግፍና መከራ እንዲቆም ቅዱስ ሲኖዶስ አሳሰበ

በካሣሁን ለምለሙ



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ በተደጋጋሚ የሚፈጸመው ግፍና መከራ እንዲቆምና በየምክንያቱ የታሠሩ ካህናትና ምእመናን ጉዳያቸው በጥንቃቄ ታይቶ ከእስር እንዲፈቱ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ባወጣው መግለጫ አሳሰበ።

የታችኛው የመንግሥት መዋቅር ባለሥልጣናት ለጥፋተኞች ከሚያደርጉት ሁለንተናዊ ድጋፍ እጃቸውን እንዲሰበስቡ ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው አሳስቦ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ ለደረሰው ጥፋትና ለወደፊትም ለሚደርሰው የሕግ ክትትል በማድረግ ችግሩን የሚከላከሉ የሕግ ባለሙያዎች ኮሚቴ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አህጉር ስብከት ድረስ እንዲቋቋም መወሰኑን አስታውቋል።

በሀገሪቱ ያለው ወቅታዊ የሰላም እጦትና አለመግባባት ለዜጎች ተረጋግቶ አለመኖር እንዲሁም ለሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት እየሆነ በመሆኑ በቀጣይ አላስፈላጊ ሁከት ውስጥ እንዳይገባ ከወዲሁ እርቅና ሰላም ማምጣት አስፈላጊ እንደሆነ ቅዱስ ሲኖዶስ አስገንዝቧል። የእርቅና የሰላም ሂደቱን የሚያስፈጽሙ ብፁዓን አባቶችም በአስታራቂነት መሰየማቸውን አስታውቋል።

አገራዊ ሰላምና አንድነት እንዲኖር የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በወሰነው መሠረት የእርቅ ሂደቱ እንዲቀጥል የፌዴራልና የክልል መንግሥታት መሪዎች ጥረት እንዲያደርጉ እንዲሁም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለሀገሩ አንድነትና ሰላም ዘብ እንዲቆም ቅዱስ ሲኖዶሱ ጥሪ አቅርቧል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አፈጻጸምን በተመለከተ ቀደም ሲል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እየተወሰኑ የተፈጸሙና ያልተፈጸሙትን በመለየት ያልተፈጸሙትን ምክንያታቸውን በመለየት ለፊታችን ግንቦት ርክበ ካህናት ውጤቱ እንዲቀርብ መወሰኑንም መግለጫው አመልክቷል።

# የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በኮሮና ቫይረስ መያዛቸው ታወቀ

የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኢሪንጅ ሰሞኑን በተደረገላቸው ምርመራ በኮሮና ቫይረስ መያዛቸውን ኦርቶዶክስ ኮግኔት ፔጅ ዘግቧል።

ቅዱስነታቸው በዚህ ሰዓት በመልካም ጤንነት ላይ እንደሚገኙ ዘገባው አስታውሶ ቤልግሬድ በሚገኘው የኮሮና ቫይረስ ሕክምና ማእከል ውስጥ ተገቢው ክትትል እየተደረገላቸው እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል።

ቅዱስነታቸው ከዚህ ቀደም በሀገራችን ኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልልና በሌሎች አካባቢዎች በቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ላይ የተፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ያወገዙ ሲሆን በሀገራቸው አምባሳደር በኩልም ለቤተ ክርስቲያን ያላቸውን አጋርነት ማሳየታቸው ይታወሳል።



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ኢሪንጀ*

# በአንድ ሐሳብ ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መቆም ይገባናል

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ፈተና ተለይቷት አታውቅም፡፡ በየዘመናቱ የሚነሡባት ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ተጋፍጣ በጸሎት እየተጋች እዚህ ደርሳለች፡፡ ጠላት ዲያቢሎስ ለዘመናት የውስጥ እና የውጭ ጠላቶችን እያስነሣ፣ መሠረቶቿን ለማናጋት ሲታገል ቆይቷል፡፡ ለዚህም ምስክሩ ደግሞ የታሪክ መዛግብቶቻችን ናቸው፡፡

ፈተናው እንደ የዘመኑ መልኩን ቀያይሮ ቢመጣም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሰው ጥፋት ግን ዓላማው አንድ ነው፡፡ ጠላቶቿ መኖርዋን ነው የማይፈልጉት፣ ማደግዋን ነው የሚጠሉት፣ ስምዋ ከመቃብር በታች እንዲሆን ነው የሚሹት፣ ጨለማቸውን ስለምታጋልጥ ብርሃንዋን ሊያጠፉ ነው የሚጥሩት፡፡ እነርሱ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት በአንድነት ሲቆሙ እኛ ግን ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ በአንድነት መቆም አልቻልንም፡፡ እነሱ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት አንድ ቋንቋ ሲናገሩ፣ እኛ ግን እንደ ባቢሎን ዘመን ሰዎች ቋንቋችን ተደበላልቋል፡፡ ከቤተ መቅደስ እስከ ዐውደ ምሕረት ፣ ሁሉም ባይሆን አንዳንዱ ከምእመን እስከ ጳጳስ አምላካዊውን ሥራ ሳይሆን የራሱን መሻት ለመፈጸም ይፈጥናል፤ አንዱ ሌላውን አይሰማም ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ስቃይ ዕለት ዕለት እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

ራሱን በደገመው ታሪክ ውስጥ ሆነን የቤተ ክርስቲያን መከራ ከአፋችን አልወርድ ከዓይናችን አልጠፋ ብሎአል፡፡ በታሪክ እንደምናውቀው ትላንት ክርስቲያኖች ለአውሬ ሲጣሉ ነበር፡፡ ዛሬ ዓለም ሠለጠነ በተባለበት በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ክርስቲያኖች በሰው መሰል አውሬዎች ታርደዋል፣ በሰው መሰል አውሬዎቸ በገዛ ሀገራቸው ላይ ስደተኛ ሆነዋል፡፡ እኛም ቆመን ይህን ክፉ ድርጊት እናያለን፡፡ በእርግጥ በቦታው ስላልነበርን እንጂ የዚህ ክፉ ድርጊት ሰለባ አካል እንሆን ነበር፡፡

በክርስቲያኑ ላይ እየዘነበ ያለው የመከራ ዶፍ ዛሬም አላበቃም፡፡ በየዕለቱ በክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለውን አዳዲስ ጥፋት እንሰማለን አሁን አሁን ሰቆቃውን የተለማመድን ይመስላል፡፡ አጀንዳውን ከማራገብ ውጪ ምንም መፍትሔ አላመጣንም፡፡ ከተሰጠን አጀንዳ ባሻገር ማየት ያቃተን ይመስላል ትላንትናም ዛሬም ነገም የምንሰማው ነገር አንድ ነው "ክርስቲያኖች ታረዱ" ከሚል ወሬ ውጪ መሬት የወረደ ፣ በተግባር የተገለጠ መፍትሔ ያስፈልጋል፡፡

ሥጋዊ ፍላጎቱን አሸንፎ ቤተ ክርስቲያንን እና ማዕተቤን እያለ አንገቱን እየሰጠ በአንድነት ለቆመ ክርስቲያን በአንድነት ቆሞ አርአያ መሆን ከአባቶች ይጠበቃል፡፡ መከራውን በድል እንሻገርም ዘንድ አባቶችን የሚያከብር፣ የሚፈራ እና የሚሰማ ትውልድ መፍጠር ራስን መለወጥ ይገባል፡፡ ዘመኑ አንዱ

ሌላውን በመንቀፍና በማንቋሸሽ የሚተጋበት፤ በዘርና በጎጥ ጎራ የሚለዩበት ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር ሰላም በአንድነት የምንቆምበት ነውና::

በየጊዜው ለሚወጡት መመሪያዎችና መግለጫዎች ተፈጻሚነት ከምእመኑ እስከ ቀዱስ ፓትርያርኩ ድረስ ‹‹እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ›› መሆንና እንደ ክርስቲያን መኖርን ይጠይቃል:: ቤተ ክርስቲያኝ ለሀገር የምትተርፍ ቤተ ክርስቲያን ናትና አጥብቀን ልንይዛት፣ በእውነት ልንመላለስባት፣ በአንድንት ልንቆምላት ያስፈልጋል::

ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ መጀመሪያ ራሳችንን ልንታደግ ይገባል:: ከውጭ ያለው በሰላም እንዲኖር በውስጥ ያለው ሰላም ይሆን ዘንድ ግድ ነው:: የቤተ ክርስቲያን ክርስቶሳዊ ሰላም ለምእመናንዋ ብሎም ለሀገር የግድ ያስፈልጋል:: በሰላም እጦት እየታወከ ላለው ምእመን መነሻው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ሰላም ነውና ከዚያ ሊጀምር ይገባል::

የሀገር ሰላም መናጋት የቤተ ክርስቲያን ሰላም መናጋት ነውና ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ሰላሙን ከቤትዋ መጀመር ይጠበቅባታል፤ ለዚህም ደግሞ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብሎ በአጸደ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰብ ሁሉ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል::

እያንዳንዱ ክርስቲያን ወደ ገዛ መንገዱ ከመሄድ ተቆጥቦ መዋቅርዋ ባማረው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አሰላለፉን አሳምሮ ሊጓዝ ይባል:: የቤተ ክርስቲያን መሠረት መናጋት የሀገር መሠረት መናጋት ነውና:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ምንም ያልጎደላት ስንዱ እመቤት በመሆንዋ በተሰናዳው መዋቅር ውስጥ በፈሪሃ እግዚአብሔር በጸሎት መትጋት የዘመኑ ትልቅ መፍትሔ ነው::

የሀገር አንድነትን ሆነ ሰላምን ለማምጣት የሰላማዊው ክርስቶስ ልጆች ለሰላም እና ለአንድነት በመቆም እየመጣ ያለውን የጥፋት እሳት ለማጥፋት በብርቱ ማገልገል ይጠበቃል፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቅዳሴዋ፣ ዝማሬዋ፣ ኪዳንዋና ሰዓታትዋ የሚነግሩን ይህንኑ እውነታ ነው:: በተግባር የሚታይና የሚጨበጥ ለቤተ ክርስቲያን እና ለሀገር የሚጠቅም ሥራ ይሠራ ዘንድ በሚደረገው መንፈሳዊ ጉዞ ሁሉ አባቶቻችን ከፊት ሆነው ሕዝቡን ሊመሩት ይገባል::

መዋቅሩን በጠበቀ አደረጃጀት እንደ አባትና ልጅ በአንድ ላይ በመቆም አንደ ነነዌ ሰዎች ከልብ ሆነን እጃችንን ወደ እግዚአብሔር ልንዘረጋ ይገባል:: ‹‹ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች›› መዝ.፷፯፥፴፩ የተባለላት ቅድስት ሀገር ናትና አምላከ ቅዱሳን ለጸሎትዋ መልስ አይነፍጋትም::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየዕለቱ ስለ ሀገር ፣ ስለ ዓለም ሰላም የምትጸልይ እንደሆነች ቢታወቅም ዛሬ ሀገራችን እንዲህ ሰላም ባጣችበት ወቅት ደግሞ አብዝታ ወደ አምላክ ልታሳስብ ይገባል:: ቅደስት ቤተ ክርስቲያን ስንል ምእመንዋን፣ ካህናትዋን፣ መነኮሳትዋን፣ ጳጳሳትዋንና ሊቃነ ጳጳሳትዋን እና በአፀደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳንን ሁሉ ማለት እንደሆነ ሁሉም ልብ ሊለው ይገባል::

ተደጋጋሚ ፈተና ሲፈራረቅባት እና የመከራ ዶፍ ሲወርድባት የከረመችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለሰባት ቀን ባወጀችው ብሔራዊ ጾም ሁላችንም እንደ ነቢዩ ዕንባቆም ‹‹አቤቱ እኔ ስጮኽ የማትሰማው እስከ መቼ ነው?›› ዕን. ፩፥፪ በማለት ልንጸልይ ይገባል፤ ያኔ አምላክ መልስ ይኖረዋል የቤተ ክርስቲያን መልስዋ ከላይ ነውና::



# ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዓመት ሁለት ጊዜያት እንዲሆን በፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ ቁጥር ፻፹፬ በተደነገገው መሠረት ምልዓተ ጉባኤው የመክፈቻው ሥርዓተ ጸሎት ከተፈጸመበት ከጥቅምት ፲፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ የተለመደውን ዓመታዊ መደበኛ ስብሰባ ሲያካሂድ ሰንብቶ ለቤተ ክርስቲያናችንና ለሀገራችን የሚበጁ ማህበራዊና መንፈሳዊ ውሳኔዎችን አሳልፎአል።

በዚሁ መሠረት፡-

፩. ለቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የቀረበው የጉባኤ መክፈቻ ንግግር የበጀት ዓመቱ የሥራ መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ምልዓተ ጉባኤው ተቀብሎታል።

፪. ለምልዓተ ጉባኤው ቀርቦ ውይይት የተካሄደበት የ፴፱ኛው አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ የጋራ መግለጫ ጉባኤው ተቀብሎ ያፀደቀው በመሆኑ ለሚመለከታቸው ሁሉ ተላልፎ በሥራ እንዲተረጐም ተወስኗል።

፫. የቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ችግር አስመልክቶ በጉባኤው ሰፊ ውይይት የተደረገበት ሲሆን ባለፈው አንድ ዓመት በአገራችን በኢትዮጵያ በቤተ ክርስቲያናችንና በክርስቲያን ወገኖቻችን ላይ የደረሰው ግፍና መከራ እንዲቆም በየምክንያቱ በክርስቲያንነታቸው ምክንያት የታሰሩ ካህናትና

ምእመናን ጉዳያቸው እየታየ ከታሰሩበት እንዲፈቱ፣ የመንግሥት የበታች ባለሥልጣናትም ለጥፋተኞች ከሚያደርጉት ድጋፍ እጃቸውን እንዲሰበስቡ ጉባኤው አጥብቆ አሳስቧል። ከዚሁ ጋር በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያን ወገኖቻችን ላይ ላለፈው ለደረሰው ጥፋትና ለወደፊትም የሕግ ክትትል በማድረግ ችግሩን የሚከላከሉ የሕግ ባለሙያዎች ኮሚቴ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አህጉረ ስብከት ድረስ እንዲቋቋም ተወስኗል።

፬. ወቅታዊ አገራዊ ሰላምን በተመለከተ ጉባኤው በሰፊው ተነጋግራል። በአገራችን ያለው ወቅታዊ የሰላም እጦት እየታየ ያለው አለመግባባት ለዜጐች ተረጋግቶ አለመኖርና ለሁከት አልፎ ተርፎ ለሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት እየሆነ በመሆኑ በቀጣይም አላስፈላጊ ሁከት ውስጥ እንዳይገባ ከወዲሁ እርቅና ሰላም ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን ጉባኤው አምኖበታል። በመሆኑም የእርቅና የሰላም ሂደቱን የሚያስፈጽሙ ብፁዓን አባቶችን በአስታራቂነት ሰይሟል።

፭. በአገራችን ኢትዮጵያ የሕዝባችን የዘመናት ድህነትና የኑሮ ጉስቁልና አስወግዶ ለአገራችንም ብልጽግና ሆነ ለሕዝባችን ዕድገት ከፍተኛ ተስፋ የተጣለበት የታላቁ ሕዳሴ ግድብ አስመልክቶ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራምፕ አካባቢያዊ ጦርነት እንዲነሣ ያስተላለፉት መልእክት አገራችን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ወይም በሞግዚትነት ለማስተዳደር የተደረገ ሙከራ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ በአጽንኦት ተቃውሞታል። የዓለምም መንግሥታትና ሕዝቦች እንዲህ ዓይነቱን ትንኮሳ እና የቅኝ ግዛት ፍላጐት እንዲቃወሙ ጥሪውን አቅርቧል።

፮. በሕገ ቤተ ክርስቲያኑ አንቀጽ ፶ የሚገኘው በአሁኑ ጊዜ ባለው የሀገረ ስብከቱ አሠራር ላይ አመቺ ሆኖ ስለአልተገኘ ከሕገ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲወጣ እና የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት እንደማንኛውም ሀገረ ስብከት ራሱን ችሎ ሊቀጳጳስ ተመድቦለት እንዲመራ ቅዱስ ሲኖዶስ ወስኗል። ከዚህም ጋር አሁን እየተሠራበት ያለው ሕገ ቤተ ክርስቲያን ከወቅቱ ጋር ተገናዝቦ መሻሻል እንዳለበት ስለታመነ ይኸው እየተሠራበት ያለው ሕገ ቤተ ክርስቲያን መርምረውና አጥንተው መሻሻል የሚገባቸውን ነጥቦች አሻሽለው ወደፊት በቋሚ ሲኖዶስ ከሚመረጡ ሕግ ባለሙያዎች ጋር ሕጉን አሻሽለው ለግንቦቱ ርክበ ካህናት እንዲያቀርቡ ሦስት ብፁዓን አባቶችን ጉባኤው መድቧል።

፯. የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አፈጻጸም አስመልክቶ ቀደም ሲል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እየተወሰኑ የተፈጸሙና ያልተፈጸሙትን በመለየት ሊፈጸሙ ያልቻሉበት ምክንያት ተገልጾ ለፊታችን ግንቦት ርክበ ካህናት ውጤቱ እንዲቀርብ ጉባኤው መመሪያ ሰጥቷል።

፰. የብፁዓን አባቶች የሥራ ምደባና ዝውውር በማስፈለጉ ቅዱስ ሲኖዶስ ያለውን ሁኔታ ከመረመረ በኋላ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ዝውውርና አዲስ የሥራ ምደባም ተካሂዷል።

፱. በምሥራቅ ጐጃም ሀገረ ስብከት በቆጋ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ተከስቶ የነበረውን የዶግማና የቀኖና ጥሰት አስመልክቶ ችግሩ በአጣሪ ልዑካን እንዲጣራ ተደርጎ በቀረበ ሪፖርት ላይ ጉባኤው ተነጋግሮ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በመንፈስ ቅዱስ ጽጽስና ተሹመናል ያሉት መነኮሳት የፈጸሙት

ድርጊት አግባብነት የሌለው ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ሆኖ ስለተገኘ መነኮሳቱ በራሳቸው የለበሱት ልብሰ ጽጻስናና የጵጵስና ቆብ አውልቀው ንስሐ ተሰጥቷቸው በምንኩስናቸው ብቻ ተወስነው በገዳሙ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዲኖሩ ተወስኗል። ከዚሁ ጋር ተፈጸመ የተባለው ዳግም ጥምቀትና ክህነት ከቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ውጭ የሆነና ቤተ ክርስቲያናችን የማትቀበለው በመሆኑ ይህን ድርጊት የፈጸሙ ሁሉ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ጉባኤው አሳስቧል።

**በአገራችን በኢትዮጵያ በዓለማችንም ጭምር እየታየ ያለው አለመግባባት፣ የጐርፍ መጥለቅለጥ፣ የበሽታ ወረርሽኝ የመሳሰሉት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ በምሕረቱ ተመልክቶ ሰላሙንና አንድነቱን ለዓለማችንና ለሕዝባችን ይሰጥልን ዘንድ ከህዳር ፩-፯ ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በመላ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አድባራት ጸሎተ ምሕላ እንዲደረግ ተወስኗል።**

፲. የኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጅ ኮሚቴ ነን ከሚሉ አባላት ጋር በተደረገ ውይይት መግባባት ደረጃ ላይ በመደረሱ ክህነታቸው የተያዘ ካህናት ክህነታቸው ተለቆ በቤተ ክርስቲያናችን መዋቅር ውስጥ የሥራ መደብ ተሰጥቷቸው እንዲያገለግሉ ተወስኗል።

፲፩. የቤተ ክርስቲያኒቱ የ፳፻፲፫ ዓ.ም. አጠቃላይ በጀት ላይ የተነጋገረው ምልዓተ ጉባኤ ከበጀትና ሂሣብ መምሪያ በቀረበው የበጀት ድልድል ላይ ተነጋግሮ ማስተካከያዎችን በማድረግ በሥራ ላይ እንዲውል አጽድቋል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ከላይ በተጠቀሱ ነጥቦች እና እንዲሁም በወቅታዊ አገራዊ ጉዳይ ላይ በስፋት ተነጋግሯል። በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የደረሰው ጐርፍ መጥለቅለቅና የአንበጣ መንጋ በበርካታ ወገኖቻችን ላይ ያደረሰው ችግር ከፍተኛ መሆኑን ጉባኤው ተገንዝቧል። በመሆኑም ሕብረተሰቡ ለተቸገሩ ወገኖቻችን የተለመደ ድጋፉን ከማድረግ ወደኋላ እንዳይል ምልዓተ ጉባኤው ጥሪውን አቅርቧል።

በአገራችን በኢትዮጵያ በዓለማችንም ጭምር እየታየ ያለው አለመግባባት፣ የጐርፍ መጥለቅለጥ፣ የበሽታ ወረርሽኝ የመሳሰሉት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ በምሕረቱ ተመልክቶ ሰላሙንና አንድነቱን ለዓለማችንና ለሕዝባችን ይሰጥልን ዘንድ ከህዳር ፩-፯ ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በመላ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አድባራት ጸሎተ ምሕላ እንዲደረግ ተወስኗል።

በመጨረሻም፡-

አገራዊ ሰላምና አንድነት አስመልክቶ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ በወሰነው መሠረት የእርቅ ሂደቱን የሚቀጥልበት ሆኖ ከዚሁ ጋር የፌዴራል መንግሥቱ የየክልል መሪዎች እንዲሁም መላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለአገራችን አንድነትና ሰላም ለልማቱና ለሕዝባዊ አንድነቱ በጋራ እንዲሠራ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን እያቀረበ የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ከጥቅምት ፲፩ እስከ ፳፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም. ድረስ ለ ፲፫ ቀናት ሲያካሂድ የቆየውን ጉባኤ በጸሎት አጠናቋል።

*ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን*

# “የአብነት መምህራን ከሌሉ ከቤተ ክርስቲያን አልፎ የኢትዮጵያ ማንነት ያሰጋኛል”

**ክፍል ሁለት**

**በመጽሐፈ ሲራክ**



መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ተክሌ

*የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል:: ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል::*

እንደአጋጣሚ ሐምሌ ፭ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በዓለ ሢመት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይከበር ነበርና እዚያ ላይ ቅኔ እንድቀኝላቸው ስለተነገረኝ በዚያ ተገኝቼ ነበር:: ለብፁዕነታቸው ቅኔ ተቀኝቼ ስወጣ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል ቤተክርስቲያን የማውቀው ጓደኛዬ ከዚያው ደብር የቅኔ መምህር የነበሩት አባት ጡረታ ስለወጡ ለመቀጠር እንድጠይቅ ጠቆመኝ እኔ ግን እጅግ ፈራሁ:: ቅዱስ ኡራኤልን የሚያህል ትልቅ ደብር ይቅርና ወደ ገጠር ለመሄድ ነበር ሐሳቤ:: በጊዜው ስምንት ተማሪዎች ይዤ በኪራይ ቤት ውስጥ ነበርኩ የነገረኝን አድምጬ ”እስኪ እግዚአብሔር ያውቃል‘ ብዬው ተለያየን::

በኋላ እሱው ነግሮ ይመስለኛል የደብሩ ጸሓፊ ሊቀ ሥዩማን ኪዳነ ማርያም ለደብረ ሲናው ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ጸሓፊ በመደወል ”መምህር አፈወርቅ ወደ ደብረ ጽጌ መምጣት ይፈልግ እንደሆን ጠይቅልኝ በእርሱ ስም ወደ ሀገረ ስብከት ደብዳቤ ጽፈናል‘ በማለት ነገረው:: ጸሓፊው ሲነግረኝ ምንም ሳላነገራግር ሀገረ ስብከት መከታተል ጀመርኩ:: በአጋጣሚ ግን ጸሓፊው ለሀገረ ስብከቱ እኔን እንደሚፈልጉ ደብዳቤ ሲጽፍ አለቃው ደግሞ በጎን ቀጨኔ ያሉት መምህር እንዲመጡ ጽፈው ኖሮ ሁለት ተቀጣሪዎች ሆነን ተገኘንና በፈተና ይለዩ ተባለ:: በኋላ ላይ እሱም ቀረና በዕጣ ይለዩ ተብሎ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ባሉበት ዕጣ ሲወጣ ለኔ ወጣና በ፯፻ ብር ደሞዝ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል አገልጋይ ሆኜ ተመደብኩ:: በጊዜው የደብረ ሲና ሕዝብ እንድቀርላቸው ጠይቀው ነበር እኔ ግን ለመመለስ ፈቃደኛ አልነበርኩም::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል ያለዎት ያገልግሎት ጊዜ እንዴት ነው?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** ደብረ ጽጌ ጥሩ የአገልግሎት ጊዜ ነው ያለኝ:: አሁን ድረስ እዚያው ነኝ:: በርግጥ ብዙ ተማሪ ባይገኝም የአብነት ትምህርቱ አለ:: እንደ ክረምት ወንዝ ክረምት ክረምት ይበዛል በጋ በጋ ደግሞ ይቀንሳል አንዳንዴም ይቋረጣል ማለት ይቻላል:: አንዳንዱ የዘመናዊው ትምህርት ይወስደዋል አብዛኛው እየሠራ ነው የሚማረው ደሞዝ የለውም:: ከሰኔ ጀምሮ ግን ዘመናዊው ሲዘጋ ብዙ ሰው ይማራል ዘንድሮ ግን በኮሮናው ምክንያት ትምህርቱ ጭራሽ ተቋርጧል::

ደብረ ጽጌ ጥሩ ጥሩ ካህናት ነበሩ፤ የማታ ስብከተ ወንጌልም ይሰጣል። እያንዳንዱ ካህን በየተራ እየገባ ወንጌልን እንዲያስተምር ተወያይተን ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው ማታ ላይ የሚሰብከውን ቀን ቀን ሲያጠና ውሎ ርእስ ጠብቆ ያስተምራል። በዓለ እግዚእ፣ በዓለ ማርያም ሲሆን ዋዜማ የሚመጡ ጉባኤተኛም ያስተምራሉ። እያንዳንዱ ካህን የራሱን ስብከት አጥንቶ መጥቶ ይሰብካል ፣ አስተያየት ይሰጠዋል በዚህም በደብሩ ላይ ያለው ካህን ሁሉ ሰባኪ ሆነ። በዚያ መነሻ ብዙዎቹ ካህናት የንስሓ ልጆቻቸውን እየሰበሰቡ በየወሩ ማስተማር ጀመሩ። ብዙዎች ወንጌልን የተማሩበት ትልቅ ቦታ ነው። አስተምረን ግን ለማስመረቅ ማኅተም አልነበረንምና ብዙ ተማሪዎች ማኅተም ካለበት ወደ ታእካ ነገሥት በአታ ለማርያም እየሄዱ እየተማሩ የምስክር ወረቀት መያዝ ጀመሩ። ስብከተ ወንጌሉ እዚያ ተመድቤ ከሄድኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ አለ እኔም አስተምራለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከጀመሩ ስንት ዓመት ሆንዎት?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ፦*** ደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ብቻ ፲፩ ዓመት አገልግዬአለሁ ከ፲፱፻፹፯ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፺፰ ድረስ ማለት ነው። ከ፲፱፻፺፰ ጀምሮ እስከ ዛሬ ደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን እያገለገልኩ ነው ያለሁት።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአብነት ትምህርት ቤት ምን ያህል ጊዜ ቆዩ?

መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ፦ በትምህርት ቤት ያሳለፍኩት ረጅም ዘመን ነው አንድ ፴ ዓመት ይሆነኛል። ቅኔ ቤት ከአምስት መምህራን ተምሬአለሁ፣ ትርጓሜ መጻሕፍት ደግሞ ከሁለት የመጽሐፍ መምህራን፣ እንዲሁም አቋቋም ከሁለት መምህራን ዘንድ ተምሬአለሁ። ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት ጠንቅቆ ማወቅ አይችልምና እኔም የተወሰነውን እና የምፈልገውን ያህል ተምሬአለሁ። ከኢሉባቦር እስከምመለስ ድረስ ለትምህርት ከሀገሬ ከወጣሁ ጀምሮ በ፴ ዓመቴ ነው ወደ ሀገር ቤት የተመለስኩት።

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** በአብነት ትምህርት ቤት መምህርነትዎ ከተማሪ ጋር የነበረዎት ግንኙነት እንዴት ነበር?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ፦*** ከተማሪ ጋር ባለኝ ግንኙነት በተለይ ወደ አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ብዙም ደስተኛ አይደለሁም የዚህ ምክንያት ደግሞ ከማስተማሩ ጋር ብዙ ነገር ስላልተመቻቸልኝ ነው። ለማስተማር እፈልግ ነበር ግን ቦታው ተመቻችቶ ተማሪ በብዛት የሚገኝበት ሲሆን ነው መንፈስም የሚነቃቃው፣ ደስም የሚለው። ዛሬ አንድ ተማሪ ነገ ደግሞ አንድ ተማሪ እየተንጠባጠበ መጥቶ ሊማር ቢል ለአንድ እና ለሁለት ተማሪ ቁጭ ብሎ መዋል ብዙም አያረካም በዚህ ምክንያት ነው በደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል የማታውን ትምህርት የጀመርኩት። አብነት ትምህርቱ ላይ ሰው ሲጠፋ ነው ካህናትን ሰብስቦ ኮርስ የመስጠት ጅማሮ የነበረው። ከምእመናን እና ከሕፃናት እንዳልለይ ሐሙስ ሐሙስ አስተምር ነበር ተማሪ አልባ ዝም ብዬ እንዳልኖር በሚል ነው።

ተማሪዎችን በሰፊው ለማስተማር ሐሳብ ነበረኝ ግን ተማሪ ስለሌለ አልተቻለም። ደብሩ አስፈላጊውን ነገር ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን አሟልቶ ቢሆን ሁሉም ሥራ እስከሆነ ድረስ ማገልገል ይቻል ነበር። እኔ ግን አሁን በብዛት አገልግሎቴ ማሕሌት መቆምና ፍትሐት መፍታት ነው። በደብረ ጽጌ እሑድን ሳይጨምር ዘጠኝ ወርኀ በዓል አለ። እሑድ አራት ጊዜ ይቆማል ከዚያ ውጪ ዘጠኙን ወርኃ በዓል በየቀኑ እየገባሁ ስቡሕ ወዉዱስ እያልኩ አገለግላለሁ። አሁን በኮሮና ምክንያት ቀረ እንጂ ፍትሐትም መንደር ለመንደር እየሄድኩ ስፈታ እውላለሁ። በአጠቃላይ ተማሪ ስለሌለ ዛሬ ላይ የኔ አገልግሎት ፍትሐትና ማሕሌት መቆም ነው።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ምናልባት ከተማ መሆኑ ተጽእኖ አድርጎ ይሆን?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** ከተማ መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው ትልቁ ምክንያት ግን የተማሪዎች የኑሮ ሁኔታ ነው። ተማሪዎች የሚበሉት ስለሌላቸው የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ወደ ሥራ እንጂ ወደ

ትምህርት አይመጡም። ጥቂት እንኳ ቢኖሩም ሙዳየ ምጽዋት እስኪያገኙ ድረስ ነው እሷም ስለማትበቃቸው ወጥተው ተጨማሪ የቀን ሥራ ይሰራሉ። ስለዚህ ከሥራ ውለው ማታ ላይ ለመማር ይደክማቸዋል ይተኛሉ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአብነት ትምህርት ቤት መምህርነት ምን ያህል ተማሪዎች አፍርተዋል የእርስዎን ፈለግ የተከተሉ እንዲሁም በተለያዩ የቤተ ክርስቲያንቱ መዋቅር ውስጥ የሚያገለግሉ አሉ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** የተቀኙ ብዙዎች ናቸው በቁጥር እንዲህ ነው ልል አልችልም። ደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ሳለሁ ቀደም እንዳልኩት የጎጃምና የጎንደር በር ስለሆነ ብዙ ተማሪዎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው እየተቀኙ ሄደዋል። ከዚህ ደብረ ጽጌ ከመጣሁ ግን የማስታውሳቸው ዘጠኝ የተቀኙ አሉ። ከዚያው ሙዳየ ምጽዋት እያገኙ የተቀኙ ወደ ዐሥር አሉ። ሌሎች ደግሞ በጋውን አቋርጠው ክረምቱን የሚጀምሩ አሉ እንደዚያ እየሆነ ቁጥራቸው ከዚያ በላይ አልሄደም ፤ መዘምርነት እንጂ ለመምህርነት ብዙ ደርሷል እንኳ ለማለት አልደፍርም።

የኔን ፈለግ የተከተለ እና እንደ እኔ መምህር የሆነ እገሌ የምለው የለም። የሚማር ተማሪ እስከሌለ ድረስ የኔን ፈለግ የተከተለ ለማለት አስቸጋሪ ነው። ምናልባት አንድ ደኅና ዘራፊ አለ ተምሮ የሄደ ተስፋ የማደርገው ነገር ግን ገጠር ነው ያለው ምናልባት እርሱ እኔን ይተካ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ቤተ ክርስቲያን እንደ እርስዎ ያሉ መምህራን እንዲበዙ ምን ማድረግ አለባት?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** መምህራን እንዲበዙ ከተፈለገ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ ያለባት በጣም አጭር ዘዴ ነው። ቤተ ክህነቱ የመምህራንን እና የተማሪን ፍልሰት ማቆም አለበት ቀድሞ በጥንቱ እንዲህ የከፋ ፍልሰት አልነበረም ጎንጅ በጎንጅ፤ ዋሸራው በዋሸራ፤ የዋድላውም በዋድላ አስመስክረው ከዚያው ቦታ ጎንጅ እና ዋሸራ ይቀመጡ ነበር። አሁን የሚፈልሱበት ምክንያት ይታወቃል። ዛሬም ለመምህራን በቂ ደሞዝ ሰጥቶ ባሉበት እንዲቀመጡ ቢደረግ መምህራን እንደሚበዙ እርግጠኛ ነኝ። የሚፈልሱትን መምህራን እና ደቀ መዛሙርት የሚፈልጉትን አሟልቶ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል። ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ ላይ ብዙ እየሠራ እንደሆነ አውቃለሁ። በበአታ፣ በጎንደር፣ በቤተ ልሔም፣ በዙር አምባ፣ በደቡብ ሌሎችም በብዙ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበሩ ብዙ ደቀመዛሙርት እያፈራ እንደሆነ እናያለን እንሰማለን ይህ እጅግ ደስ የሚል ሌሎችም ሊከተሉት የሚገባ መልካም ተግባር ነው።

ይህ በጎ ተግባር መቀጠል መስፋት አለበት አዲስ አበባ ላይ ያሉ መምህራን ደቀ መዛሙርትን እንዲያስተምሩ ቢደረግ ጥሩ ነው። ጉባኤ ከሌለ ምን ይጠቅማል? ጉባኤያት በምንጭ ይመሰላሉ፤ ምንጭ ከከርሠ ምድር ካልወጣ ይቆማል ምንጩ እየበዛ ሲሄድ ደግሞ ፈሳሽ ይሆናል፤ ፈሳሹ እየበዛ ሲሄድ ወራጅ ይሆናል ። ምንጩ ደጋውን፣ ወራጁ ወይና ደጋውን፣ ፈሳሹ ቆላ ደጋውን አጠጣ ማለት ነው ነገሩ የተያያዘ ነው። እንደዚህ ጉባኤያት ምንጭ ከሆኑ ከምንጭ የሚወጣው ፈሳሽ ምንድነው መምህራን ናቸው ማለት ነው። ከጉባኤ የሚወጡ መምህራን ናቸው። ወራጁ ቆላውን የሚያጠጡ መጻሕፍት ናቸው። ከመምህራን የሚወጡ መጻሕፍት ማለት ነው ተያያዥ ነው። ያ ምንጭ እስካለ ድረስ መምህራንም አሉ መጻሕፍትም አሉ። ምንጩ ከደረቀ ግን ስቡሕ ወዉዱስ ብሎ የሚቆም ወይም አሐዱ ብሎ የሚቀድስ ይቅርና ተንሥኡ ጸልዩ የሚል ደቀ መዝሙር አናገኝም ይህ የታወቀ ነው።

ዛሬ የምናገኛቸው አባቶቻችን ጳጳሳት በቅዳሴው በቅኔው፣ በአቋቋም፣ በመጻሕፍት ትርጓሜና በሌሎቹ የአብነት ትምህርት ቤት ውስጥ አልፈው እዚህ የደረሱ፤ ስለ እመ ብርሃን ብለው ከጉባኤ የወጡ ሊቃውንት እንጂ ቤተ ክርስቲያን ዝም ብላ ያመጣቻቸው አይደለም። ስለዚህ እነዚህ ምንጮች፣ ፈሳሾች፣ ወራጆች እንዳይደርቁ ጉባኤያትን ማጠናከር ነው። አባቶች ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርና ምንጭ ናቸውና። ቤተ ክርስቲያን

እነዚህን የዕውቀት ምንጮች በደንብ ይዛ የሚገባቸውን እየሰጠች እንዲያስተምሩ የምታደርግ ከሆነ ከሥር እየተተካ ይሄዳል ማለት ነው፡፡ አሁን እንደምናየው ብዙ ዕድሜውን በአብነት ትምህርት ቤት ቆይቶ ሲወጣ ቤተ ክርስቲያን ደሞዝ ከፍላ በሚገባው ቦታ ተቀምጦ እንዲያገለግል ማድረግ አለባት፡፡ ይህ ካልሆነ ከ፳ እና ፴ ዓመት በኋላ ሊሆን የሚችለው ነገር ካሁኑ ያሰጋኛል፡፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአብነት ትምህርት ቤቶች ምንጫቸው ከደረቀ፣ መምህራን ከሌሉ ከቤተ ክርስቲያን አልፎ የኢትዮጵያ ማንነት ያሰጋኛል፡፡ ሀገራቸው እንደፈረሰ እንደ የመን እንደሌሎች ሀገሮች እንዳትሆን እሰጋለሁ፡፡ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ አደጋ ተጋርጦ ነው ያለው፡፡

ይህን መቋቋም ካልቻልን ትምህርት ቤቱን አባዝተን ተማሪዎች እንዲበዙ ካልተደረገ እና ካልተጠናከሩ "ሁሩ ወመሀሩ' የሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ካልተላለፈ በስተቀር ሁላችንም ደሞዝ ብቻ እያገኘን ያለማስተማር የምንቀመጥ ከሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያስፈራል፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** መጻሕፍት እንዳሳተሙ ይታወቃል ምን ያህል ናቸው? ይዘታቸውስ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ፦*** መጻሕፍቱ እንዲህ ዝም ብሎ ከመቀመጥ የተጻፉ ናቸው፡፡ ልብም ኅሊናም ስለማያርፍ ነው እንጂ ተሰጥኦ ኖሮኝ ወይም አዋቂ ሆኜ አይደለም የጻፍኩት፡፡ ግስ ወርዶ ሲያልቅ ቅኔ ተዘርፎ ሲያልቅ የሚመጡትን ሐሳቦች ችሎታ ያላቸውን ልጆች ኑ ጻፉ እላለሁ ይጽፋሉ ያቺ ተቀመጣለች ከጊዜ በኋላ ደግሞ ሌላ ሐሳብ ሲመጣ እንዲሁ ይደረጋል ያቺን አጠራቅሜ ነው መጽሐፍ ያደረግሁት፡፡

ለኅትመት የበቁት አምስት ያህል መጻሕፍት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው መጽሐፍ መጽሐፈ ታሪክ ወግስ የሚል ነው፡፡ በቆሎ ትምህርት ቤት የተማሪውን ችግር ለማቅለል የጻፍኩት ነው፡፡ የቆሎ ትምህርት ቤት ግስ በእጅ ተጽፎ ነው የሚጠናው ፤ መጻፍ የማይችል ሰው ከፍሎ ለማጻፍ ገንዘብ ይቸገራል በዚያ ላይ ግሱ ላይ ታሪክም ስላለ የተማሪን ችግር ለመፍታት ነው የዕለቱን ታሪክ እና ግሱን ለማጥናት እንዲመቻቸው አድርጌ የጻፍኩት፡፡ በዚህ መነሻ ነው በመጀመሪያ ግሱን ወደ አማርኛ በመተርጎም፣ ሊቃውንት ጥንት በእጅ ጽፈውት የነበረውን ግእዙን እንዲሁ ክብረ በዓል ደግሞ ከልደታ እስከ ፴ ቀን ያሉተን በአጠቃላይ አርስተ ግስ የቅኔ ዜማ ልክ፡ የአእመረን እርባታ እነዚህ ተሰብስበው ነው መጽሐፈ ታሪክ ወግስ መጽሐፍ የተጻፈችው፡፡

ሁለተኛዋ ትምህርተ አበው ወውሉድ የምትል አነስተኛ መጽሐፍ ስትሆን የአባቶች ትምህርት ለልጆች የምትል ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣ አምስቱን አእማደ ምሥጢር፣ ለሕፃናት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ታሪኮችን እንዲሁም የደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የያዘች መጽሐፍ ናት፡፡

ሦስተኛዋ መዝሙረ ማሕሌት ወቅዳሴ የምትል መጽሐፍ ስትሆን የሰባቱን ዕለታት እና የዐሥራ ሁለቱን ወራት አጠቃላይ ታሪክ የያዘች መጽሐፍ ናት፡፡ ምስባኩ፣ የወንጌሉ እና መልእክታቱ፣ የዘመኑ ታሪክም ዘመነ ጽጌ፣ ዘመነ መስቀል፣ ዘመነ ፍሬ እና ዘመነ ዮሐንስ በሚል ተከፋፍለው የተጻፉባት መጽሐፍ ናት፡፡

አራተኛዋ መጽሐፍ ቤተሰብና እንስሳት የምትል መጽሐፍ ናት፡፡ ቤተሰብ እና እንስሳት ለየት ያለ ታሪክ ያላት ሲሆን የሰውን ከልደት እስከ እርግና ያለውን ታሪክ በዕድሜ ደረጃ በመከፋፈል፤ እንዲሁም ስለ እንስሳት የሚበሉና የማይበሉትን እንስሳት በመዘርዘር ዘሌዋውያን ፲፩ ላይ ካለው ጋር በማጣቀስ የጻፍኩት መጽሐፍ ነው፡፡

አምስተኛው መጽሐፍ ሐረገ ትውልድ ዘክርስቶስ የሚል ነው፡፡ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ ያለውን ትውልድ ነው የሚተርከው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዘመነ ሐዋርያት፣ ዘመነ ሐዋርያን አበው፣ ዘመነ ሰማዕታት፣ ዘመነ ሊቃውንት. . . ወዘተ አካቶ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ ከላይ ከጠቀስኳቸው መጻሕፍት በተጨማሪም እግዚአብሔር ቢፈቅድ ለኅትመት የተዘጋጁ ሁለት መጻሕፍትም አሉኝ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በሕይወትዎ፣ በአገልግሎት ዘመንዎ የገጠምዎን ጥሩም ሆነ መጥፎ የሚሉትን እና የሚያስታውሱት ቢነገሩን?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** ጥሩና መጥፎ የምንለው ያው የተፈራረቀብን ደስታና ኃዘን ማለት ይመስለኛል። በጣም የተደሰትኩበትን ጊዜ አላስታውስም ሐዘን ግን ከልቤ ጠፍቶ አያውቅም። በተለይ የዚህን ዓለም ከንቱነት ሳስብ ፣ "ሰውና እንጨት ተሰባሪ ነው' የሚለው ከኅሊናዬ ሲመላለስ ሐዘን ካልሆነ በስተቀር ደስታ ወደ ሐሳቤ መጥቶ አያውቅም። ሆኖም መጀመሪያ ያዘንኩበት ቀን ልጅ ሆኜ ፍየል ስጠብቅ ቦምብ የመታኝ ቀን ነው። የምንጠብቃቸው ፍየሎች ጠፍተውብን ከጓደኞቼ ጋር ባድማ ውስጥ ስንፈልግ በጨርቅ የተጠቀለለ ነገር አግኝተን ከኛ ከፍ የሚል ልጅ ነበር ምንነቱን ለማወቅ በድንጋይ ሲቀጠቅጥ ፈነዳ እኔ ከእርሱ ጀርባ ነበርኩና ፊቴ ላይና እጄ ላይ ጉዳት ደረሰብኝ ያ ጠባሳ ትቶ አልፎአል ሐዘኑ ግን ከልቤ አይጠፋም።

እንዲሁም ዳሃና ዓምደ ወርቅ ልዩ ቦታው ጉራምባ ጊዮርጊስ የኔታ ታምራት ከሚባሉ ሊቅ ዘንድ እየተማርኩ ሳለ ደግሞ ወረርሺኝ ገብቶ ነበር ። በዚያ አካባቢ የወረርሺኙን ስም "ሸዋ' ይሉታል በመጀመሪያ በዚያ ወረርሽኝ ምክንያት ጓደኛዬ ሞተ። እኔም የወረርሽኙ ዕጣ ፋንታ ደርሶኝ ከሞት ተርፌአለሁ። ተማሪዎች ተራራ ላይ እንደ ጎጆ ተክለው "ቀሳ'ይባላል በዚያ የተወሰነ ጊዜ ቆይቼ ጓደኞቼ አስታማሚ ሆነው እየረዱኝ ድኜ ወጥቻለሁ። እንደሚታወቀው የአብነት ትምህርት ቤት እያለን አባት እናት ስለሌለ ተማሪው ነው እርስ በርሱ የሚረዳዳው። ያንን ችግር በአብነት ትምህርት ቤት ጓደኞቼ እርዳታ አልፌዋሁ።

ሌላው የኢህአዴግ ሠራዊት ሰቆጣን ሲቆጣጠር እኔ ከአባ ዓለሙ ጋር ነበርሁ እየተማርኩ ምሽቱን ከደርግ ጋር ሲዋጋ አደረና ንጋት ላይ ከተማዋን ተቆጣጠረ። ጥዋቱን በየመንደሩ ሲዞር እኔ ያለሁበትን ቤት መጥቶ በሩን በመደብደብ አስከፈተኝ የኔታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ነበርና እኔን ይዘው ሊሄዱ ይጎትቱኝ ጀመር ሰዎች ልጅ ነው ተማሪ ነው ብለው ሊያስጥሉኝ ቢሞክሩም የደርግ ወታደር ነው ይኸው ጠባሳ አለው እጁ ሁሉ ተመትቷል ብለው እምቢ ብለው ሰውን ሁሉ ያስጨነቁበት ጊዜ መቼም አልረሳውም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ቀረ የሚሉትና የሚጨምሩት ወይም የሚያስተላልፉት ነገር ካለ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** የምጨምረው የለም ጠርታችሁ ስለጠየቃችሁኝ ከሕይወት ልምዴ እንዳካፍል ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ።ዛሬ ዛሬ ዙሪያው በጣም አስቸጋሪ እየሆነ ነው ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ተግታ ልትሠራ ይገባታል። ሁላችንም ከቤተ ክርስቲያን የተወለድን፣ መግቢያችን፣ መጠጊያችን እርስዋ ናት ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን እንድትሰፋ እና እንድትበዛ ተግተን ልንሠራ ይገባል። የቤተ ክህነቱም ሆነ የማኅበሩ የቴሌቭዥን ጣቢያ በዚህ ረገድ ጥሩ እየሠራ ይገኛል። አሁንም አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ ሕይወታቸው አስተማሪ የሆኑትን ሊቃውንትን ብታቀርቡ ጥሩ ነው። ብዙ የተበላሹ ነገሮች ሊስተካከሉ ይችላሉና።

በቅኔው፣ በግእዙ በኩል የሐዲሳቱ ሊቃውንት ቢቀርቡ ብዙ ያስተምራሉ የጠመመውን ያቃናሉ። በተለይ ግእዝ ሞቷል፣ ተቀብሯል የሚሉቱ ብዙ ናቸው እኔ ግን ይበልጥ እየጠፋ ያለው ቅኔ ነው እላለሁ። የሚያስተካክል የሚያርም አባት ቁጥር እየመነመነ ነውና፡ ለምሳሌ አቋቋም ቢበላሽ ተው እንዲህ አይደለም የሚል ብዙ ነው ሊቃውንቱ ማሕሌቱ ላይ፤ ዜማም ሲሰበር እንደዚሁ የሚያቀናው ብዙ ነው። ቅኔ ግን ሞያው ይቅርና ዜማው ሲሰበር ተው የሚል የለም። የዚህ አገልግሎት አነስተኛ እንደሆነ እናውቃለን።

በተለይ የግእዝ መምህራንን አቅርባችሁ የግእዝ የት መጣ ገለጻ እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል። ጥንታዊ የመጀመሪያው በመሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሐዲሳትም፣ የብሉያትም፣ የሊቃውንቱም፣ የመጽሐፈ መነኮሳቱም ምንጩ ስለሆነ የቅኔው እና የግእዙ ሊቃውንት እንዲበዙ ብታደርጉ በእውነቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ ወደፊት ትንሣኤዋን ታገኛለች ብዬ አስባለሁ። አምላካችን እግዚአብሔር እናንተንም ይጠብቃችሁ ማኅበሩን ያስፋ ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅ ኢትዮጵያን ያስፋ እግዚአብሔር ይስጥልን አመሰግናለሁ።

# “ወራሪ እየተባልን ከመገደልና ከመሰደድ ወጥተን የሀገር ባለቤትነታችንን ልናረጋግጥ ይገባል”

*አቶ ፋንታሁን ዋቄ*

*በማኅበረ ቅዱሳን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ)*

**በካሣሁን ለምለሙ**

## ክፍል ሁለት

*የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል። በጥሞና ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው።*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** የዘር ማጥፋት መከላከያ ተቋምና ሌሎች ማኅበራት በሀገር ውዳድና በቤተክርስቲን አባቶች መቋቋሙ ይታወሳል። ስለሆነም ማኅበረ ቅዱሳን ከእነዚህ ማኅበራት ሕብረት ጋር ያደረገው ቅንጅታዊ አሰራር አለው ማለት ይቻላል?

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ፡-*** አንዳንዱ ማኅበራት በቅርቡ ቢመሰረቱም ወቅታዊና አስፈላጊዎች ናቸው። የማኅበራቱ ምስረታ ዘገየ ቢባል ነው እንጂ አስፈላጊነታቸው ግን የሚያጠራጥር አይደለም።

ማኅበረ ቅዱሳን በጠቅላላ ጉባኤ እየወሰነ የሚሠራቸው ሥራዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የማኅበሩ አባላት በቀናኢነት ባሉበት አካባቢና በተሰማሩበት ሙያ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ። በቅርቡ ከተመሰረቱት ማኅበራት ጋር በተለይም “ከዘር ማጥፋ ተቋም” ጋር ይፋዊ የሆነ የሥራ ግንኙነት እስካሁን ድረስ የለንም። ነገር ግን በሽማግሌዎች ማኅበራትም ሆነ በዘር ማጥፋት መከላከያ ተቋሙ ውስጥ የእኛው ደጋፊና አባላት ይኖራሉ። እነዚህ አካላት ለቤተ ክርስቲያንና ለምእመናን ይጠቅማል ያሉትን ሥራ ከሠሩ በአንድም በሌላ ማኅበሩ ሠርቷል ማለት ነው። ለወደፊቱ ግን ማኅበረ ቅዱሳን በይፋ ከእነዚህ ማኅበራት ጋር በጋራ የሚሠራ ይሆናል፤ እንመካከራለን፤ እንደጋገፋለንም። እነዚህ ማኅበራት በቅርቡ የተቋቋሙ በመሆናቸው ጠንካራ የሆነ መዋቅራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ጊዜ ወስደን ጠንክረን እንሠራለን።



*አቶ ፋንታሁን ዋቄ*
*በማኅበረ ቅዱሳን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ*

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ቤተ ክርስቲያን በሚደርሱ ጥፋቶች ምክንያት በተደጋጋሚ መግለጫ ከማውጣቷ ባለፈ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለማስቆም ምን ብትሠራ መልካም ነው ይላሉ?

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ፡-*** ቤተ ክርስቲያን እካሁን ድረስ ከላይ እስከ ቤተሰብ ድረስ ያለውን መዋቅሯን የምትገለገልበት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት የምትሰጣቸውን ምእመናን መጠበቅ ሳትችል መንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ መስጠት ምእመናንንና ቤተክርስቲያንን ለተደራራቢ ጥፋት ማጋለጥ ነው። በምእመናንና በካህናት ላይ ንቅናቄ መፍጠር እና በፍጥነት ማደራጀት ያስፈልጋታል። ካህናትና ምእመናን ዘመኑ መቀየሩን እንዲያስተውሉ ማድረግ፤ ኦርቶዶክሳውያንን ሀገር አልባ የማድረግ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም መኖሩን ለምእመናንና ለአገልጋዮች ማስገንዘብ ያስፈልጋል። ሀገራችንን ከመነጠቃችን በፊት ቤተክርስቲያን ለልጆቿ ያለውን እውነታ መልሳ መላልሳ ማስገንዘብ አለባት። ፖለቲካውንም በባዕዳን እጅ ከመነጠቃችን በፊት መልሶ የራስ ማድረግ መታሰብ ያለበት ትልቅ ጉዳይ ሊሆን ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን ለምእመናንዋ፣ ለአገልጋቿ በተግባር የተደገፈ ሁለንተናዊ ሥልጠናዎችን ማመቻቸት አለባት። ወራሪ እየተባልን ከመገደልና ከመሰደድ ወጥተን የሀገር ባለቤት መሆናችንን በፍጥነት ልናረጋግጥ ይገባናል።

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ማኅበረ ቅዱሳን እንደ ቤተ ክርስቲያን አጋርነቱ ምን እየሠራ ይገኛል? በቀጣይስ ምን ለመሥራት አቅዷል?

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ፡-*** ማኅበረ ቅዱሳን እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራው መኅበር በመሆኑ ያቅሙን ያህል እየለፋ እየሠራ ይገኛል። ማኅበሩ በዋናነት እየሠራ ያለው ሰውን ነው። የሰው ልጅ በሃይማኖት፣ በምግባር እንዲጸናና ዙሪያውን በአግባቡ እንዲረዳ የማድረግ ሥራዎችን ለረጅም ጊዜ ሲሠራ ቆይቷል። ምእመናን በሃይማኖታቸው እንዲጸኑ፣ መልካም እንዲሆኑ፣ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸውና፣ ሀገራቸውን እዲወዱ እንዲጠብቁ የማድረግ አገልግሎቶችን እፈጸመ ይገኛል። በአገልግሎት መሀል ፈተናዎች ሁሌም ይኖራሉና ፈተናዎችን ከመቀነስና ከመከላከል ረገድ ከሞላ ጎደል ማኅበሩ ሥራዎችን ሠርቷል። ስለሆነም ምእመናንና የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ተረድተው በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ጸንተው ለዘላለም እንዲቆዩ ያስፈልጋል።

ምእመናን በዚህ ወቅት በተለያዩ ችግሮች በተሰደዱና በተፈናቀሉ ጊዜ በሥነ ልቦናና በረሀብ ተጎጂዎች እንዳይሆኑ ባለጸጎችን በማስተባበር አስፈላጊው ሁሉ ሰብአዊ ድጋፍ በማኅበሩ በኩል እየተደረገ ይገኛል። ምእመናን ተሥፋ ቆርጠው እንዳይሰደዱና ሃይማኖታቸውን እንዳይለውጡ በማኅበሩ በኩል ያላሰለሰ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ምእመናንን እያሳደዱ ወደ አንድ ቦታ በመሰብሰብ በቀጣይ "ጂሃዳዊ ጦርነት" ማወጅ አላማቸው እንደሆነ በመረዳት፤ ማኅበረ ቅዱሳንም ምእመናን ባደጉበትና በኖሩበት አካባቢ ተረጋግተው እንዲቆዩ የማድረግ ሥራዎችን እየሠራ ነው። ለወደፊቱም ከዚህ የተሻሉ ሥራዎችን ይሠራል።

ማኅበረ ቅዱሳን ለወደፊቱ ከቤተ ክርስቲያን ልዩ የሆነ ሥራ ባይሠራም ቤተ ክርስቲያን የምትሰጠውን የልጅነት ሥራ ተቀብሎ ለመሥራት ግን ቁርጠኛ ነው። ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን ከጥቃት የምትጠብቅበትን መዋቅር

ሠርታ መንቀሳቀስ ከቻለች ማኅበሩ ቀዳሚ ተሳታፊ ለመሆን ዝግጁ ነው። አንዳንድ ጊዜ ማኅበረ ቅዱሳንን የሁሉ ነገር መፍትሔ አድርጎ መውሰድ ምእመናንን ማሳሳት በመሆኑ ተገቢ አይደለም። ማኅበሩ ማድረግ የሚችለው የድርሻውንና የአቅሙን ብቻ ነው። ምእመናን፣ ቤተ ክርስቲያንና ካህናት አገልጋዮች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ድርሻ አላቸው። ሀገር ላይ ችግር የለም ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ ዋጋ ያስከፍላልና በማንኛውም ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በምትዘረጋው መዋቅር ውስጥ ማኅበሩ ተሳትፎውን በማሳደግ የራሱን ድርሻ የሚወጣ ይሆናል።

በክልል በክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ጥቃት ጨርሶ ማጥፋት ባይቻልም መከላከል ግን ይቻላል። በኦሮምያ ክልል የክርስቲያን ዘር የተባለን ሁሉ ጨርሶ ለማጥፋት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት እንዳሉ ከዚህ ቀደም የተፈጸሙት ተግባራት አመላካቾች ናቸው። በመሆኑም ይህንን ተግባር ከማውገዝ በዘለለ ስልታዊና ሕጋዊ አካሄዶችን ተከትለን በትኩረት መሥራት ይጠበቅብናል።

የኦሮምያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትም በየጊዜው መግለጫ እያወጣ የተፈጠረውን ችግር ማቃለል ሳይሆን ሰዎች ያለ አግባብ እንዳይገደሉ፤ እንደይፈናቀሉ እና ሀብት ንብረታቸው እንዳይቃጠል እንዳይዘረፉ መሥራት አለበት። ችግሮች ከደረሱ በኋላም የተጎዱ ወገኖችን ማፅናናት፣ ማቋቋም፣ ካሳ መክፈል፣ የሕይዎት ዋስትና መስጠት እንዲሁም ችግር በፈጠሩ የመንግሥት አካላትም ሆነ ግለሰቦች ላይ ተመጣጣኝ የሆነ ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። መንግሥት እስኪደርስላቸው ድረስ ምእመናን ቀድመው ያላቸውን አቅም አሟጠው የራሳቸውን ደኅንነት ሊጠብቁ ይገባል። ከዚህ በኋላ ምእመናን "መንግሥት ይደርስልናል" ብለው መዘናጋት የለባቸውም። ‹‹መንግሥት" የተባለው ቆሞ የሚያሳርድ ከሆነ ለወደፊቱ ሰላምን ያመጣል ብሎ መተማመን ከንቱ ድካም ነው።

በክርስቲያኖች ላይ እየተፈጸመ ያለው ጥቃት መዋቅራዊና ሥርዓታዊ በመሆኑ መደረግ ያለበት ነገር ሁሉ መደረግ አለበት። ኦርቶዶክሳውያንን ለማጥፋት የደህንነትና የጸጥታ መዋቅር እያለ ደህንነት ሊሰማን ስለማይችል በደህንነቱም በፀጥታ መዋቅሩም ዘልቀን እስካልገባን ድረስ ሞታችን ሞት ሆኖ ስለሚቀጥል በተጠቀሱት ሁለት ዘርፎች ላይ የተሻለ ሥራ መሥራት አለብን። ከዚህ ሥራ ያነሰ በሙሉ ኦርቶዶክስንና ኦርቶዶክሳውያንን ያጠፋል።

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር!*

**ኦርቶዶክሳውያንን ሀገር አልባ የማድረግ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም መኖሩን አገልጋዮችና ምእመናን መገንዘብ አለባቸው።**

# ጸሎት በቤተ ክርስቲያን

በቀሲስ ዘክርስቶስ ፀጋዬ

*የተወዳጃችሁ የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን አላችሁ? መልካም፤ እግዚአብሔር አምላካችን የተመሰገነ ይሁን። በቤታችሁ ሆናችሁ ትምህርታችሁን በጥሞና ተከታተሉ!*

ልጆች ባለፈው ትምህርታችን ላይ ጸሎት በቤታችን መጸለይ እንዳለብን አስተምረናችኋል፤ አሁን ደግሞ ጸሎት በቤተ ክርስቲያን ስንጸልይ ምን ማድረግ እንዳለብን እንመለከታለን።

የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት መንገድ መካከል አንዱ ጸሎት ስለሆነ በየትኛውም ቦታ ሆነን የምንጸልየውን ጸሎት እግዚአብሔር አምላክ ይሰማል፤ ይሁን እንጂ የተመረጡ የተቀደሱ ቦታዎች አሉ። ይኸውም በቤታችን ውስጥ የተለየ የጸሎት ቦታ በማዘጋጀት መጸለይ እና በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ከካህናት አባቶች እና ከምእመናን ጋራ በኅብረት የሚጸለይባቸው ናቸው።

ልጆች ጸሎት በቤተክርስቲያን በዘፈቀደ(ያለ ሥርዓት) የሚከናወን ሳይሆን ራሱን የቻለ ሥርዓት ያለው ነው። ይህም ከመጸለያችን በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅብናል። ማድረግ የሚገባንን ዝግጅት ለመረዳት ያስችለን ዘንድ በሁለት ወገን ከፍለን እንመለከተዋለን። ከእነዚህም አንዱ ውጫዊ (አፍአዊ ዝግጅት) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውስጣዊ ዝግጅት ነው።

በዛሬው ትምህርታችን ውጫዊ (አፍአዊ ዝግጅቶች) ውስጥ የሚጠቃለሉትና ማድረግ የሚገባንን እንመለከታለን።

## ሀ. መታጠብና አለባበስን ማስተካከል

ከመኝታ ተነስተን ወደ ጸሎት ከመሄዳችን በፊት እጅንና ፊትን መታጠብ ያስፈልጋል ነጠላችንን መስቀለኛ ማጣፋት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔድ ሴቶች ረዥም ልብስ መልበስ (ሴቶች) በጸሎት ጊዜ ጸጉርን መከናነብ ቀሚስ መልበስ ይገባል።

## ለ. መብራት ማብራት

“መልካሙን ሥራችሁን አይተው፥ በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲሁ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ” እንደተባለው ጧፍ ወይም ሻማ አብርተን ስንጸልይ የሚበራውም መብራት የእግዚአብሔርና የቅዱሳኑን ብርሃንነት ያስታውሰናል። ቅዱሳን መላእክት(ጻድቃን ፣ሰማዕታት፣...) በዙሪያችን እንዳሉም ያሳስበናል። (ማቴ. ፭፥፲፮)

## ሐ. አቋቋም (ቀዊም)

ለጸሎትና ለምስጋና በምንቆምበት ጊዜ በቅዱሳን ሥዕላት ፊት በመቆም እንደ ሥዕሉ ባለቤት የሥላሴ (የእግዚአብሔር ወልድ) ከሆነ የአምልኮት፣ የእመቤታችንና የቅዱሳን ከሆነ የጸጋ የአክብሮት ስግደት በመስገድና በመሳለም ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ፍቅር እንገልጥባቸዋለን።

ዓምድ (ቋሚ) ሳይደገፉ፣ መቋሚያ ሳይዙ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መቆም ይገባል። “በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ” በማለት ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ እንደገለጸው እግርን አጣምሮ መቆም አይገባም። ካልታመሙ ለመቆም የማያስችል ችግር ከሌለ ተቀምጦ( ተኝቶ) መጸለይ አይገባም። (መዝ. ፭፥፫)

ቅዱሳን ሥዕላት ከሌሉ ፊትን ወደ ምሥራቅ አድርጎ ወደ ግራና ቀኝ ሳያዩ መቆም እጆቻችንን ከሰውነታችን መስቀለኛ አድርጎ በመዘርጋት /መጸለይ ይገባል/። በቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ “በሌሊት በቤተ መቅደስ እጆቻችሁን አንሡ፥ እግዚአብሔርንም አመስግኑት” (መዝ.፻፴፫፥፪) በማለት ተናግሯል።

## መ. ዓይንን ወደ ሰማይ ማንሳት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረን ዓይንን ገልጦ ወደ ሰማይ አቅንቶ መጸለይን ነው፡፡ ለዚህም አልዓዛርን ባስነሳው ጊዜ ዓይኑን ወደ ላይ በማቅናት ጸልዮአል፤ እንደዚሁም አምስት እንጀራና ሁለቱን ዓሳ (ጎብስቱን) አበርክቶ ሲያበላ ያደረገውን ምሳሌ በማድረግ እኛም ዓይናችንን ወደ ሰማይ ወደ ቅዱሳት ስዕላት በማቅናት በመመልከት መጸለይ ይገባናል፡፡ (ዮሐ.፲፩፥፵፩፣ ፲፯፥፩)

## መ. ማማተብ

ጸሎት ሲጀመርና ሲፈጸም አመልካችን ጣትን ከሌሎች ጣቶች ጋር አመሳቅሎ በትእምርተ መስቀል አምሳል ከላይ ወደ ታች ከግራ ወደ ቀኝ በማድረግ ሳይፈጥኑና እጅን ሳያወራጩ ረጋ ብሎ ማማተብ ይገባል፡፡

በጸሎት ላይ መስቀልን የሚያነሳ ቃል ስንጠራም ማማተብ ያስፈልጋል፡፡

ስናማትብ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤ አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፊቴንና መላ ሰውነቴን አማትባለሁ በማለት በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን" እያልን ነው፡፡ ስናማትብም የዲያብሎስ ሠራዊትን እናርቅበታለን የጠላትን ኃይል ድል እንነሳበታለን፡፡

## ሠ. አስተብርኮ (ስግደት)

ለጸሎትና ለምስጋና በምንቆምበት ጊዜ በቅዱሳን ሥዕላት ፊት በመቆም እንደ ሥዕሉ ባለቤት የሥላሴ ከሆነ የአምልኮት፣ የእመቤታችንና የቅዱሳን ከሆነ የጸጋ የአክብሮት ስግደት በመስገድና በመሳለም ለሥዕሉ ባለቤት ያለንን ፍቅር አንገጥላቸዋለን፡፡

በጸሎት መጀመሪያና መጨረሻ ጉልበትን በማስተብረክ በመስገድ መጸለይ ይገባል፡፡ ስግደትን የሚያነሣ አንቀጽ ሲደርሱም ለእግዚአብሔር መስገድ ያስፈልጋል፡፡ በዕለተ ሰንበት (ቅዳሜ እና እሑድ)፣ በበዓለ ሃምሳ በበዓለ ወልድ በሀያ ዘጠኝ፣ በእመቤታችን በሀያ አንድ፣ በቅዱስ ሚካኤል በዐሥራ ሁለት፣ ሥጋና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ በእነዚህ ቀናት ጉልበት ምድር አስነክቶ መስገድ አይገባል፡፡ የዚህም ምክንያት ዕለታቱ በዓል በመሆናቸው በአንደበታችን ማመስገንና መዘመር እንጂ በጉልበታችን ስግደት አይፈቀድም፤ ቁርባን ከጠቀበልን በኋላም የጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም በውስጣችን ስለሚኖር በሰውነታችን ክቡር ስለሚሆን መሬት መንካት የለብንም፡፡

## ሰ. ጸሎት አለማቋረጥ

ጸሎትን አቋርጦ ከማንም ሰው ጋር ፈጽሞ በቃልም ሆነ በምልክት መነጋገር አይገባም፡፡

ጸሎቱን የሚያቋርጥ ችግር ከገጠመን አባታችን ሆይ ብለን በማሳረግ ጸልየን ንግግራችንን ስንፈጽም ወደ ጸሎት ስንመለስ በድጋሚ አባታችን ሆይ ብለን ያቋረጥነውን መቀጠል ይኖርብናል፡፡

ጸሎት መጸለይ ከጀመርን ጀምሮ አንድ ቀን መተው በሌላ ቀን መጸለይ ሳይሆን ከጀመሩ አለማቋረጥ ተገቢ ነው፡፡

እንግዲህ ልጆች ጸሎት ንጹሕ ቅዱስ የሆነውን እግዚአብሔርን የምንነጋገርበት እንዲሁም አምላካችን እግዚአብሔር ያከበራቸውን ቅዱሳንን የምናናግርበት እንዲያማልዱን የምንማጸንበት መሆኑን አውቃችሁ በንጽሕናና በሥርዓት መጸለይ፣ ከመጸለያችሁ በፊትና በጸሎት ጊዜ መደረግ ያለበትን ዝግጅት በተማራችሁት መሠረት በሚገባ መፈጸም ይጠበቅባችኋል፡፡

ልጆች እስከ ዛሬ ጸሎት ያልጀመራችሁ ካላችሁ ጀምሩ፤ የጀመራችሁ ደግሞ ሳታቋርጡ አጠናክራችሁ ቀጥሉበት፡፡ ይህንን ስታደርጉ አምላካችን እግዚአብሔር ይወዳችኋል፡፡

በመጨረሻም በሚቀጥለው ትምህርት እስክንገናኝ መልካሙንና የተወደደውን ነገር ሁሉ እንመኝላችኋለን፤ ደኅና ሰንብቱ!

# ገንዘብ እንጂ ምግብ የማይፈልጉ ነዳያን

እህተ ሚካኤል ከጎፋ ገብርኤል

ምጽዋት ለሌሎች ቸርነትን ማድረግ በኢትዮጵያ በተለይም ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስያን ምእመን እጅግ የለመደ ነው። "ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ በደቀ መዝሙሬ ስም ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋውን አያጣም" ማቴ ፲፥፵፪ የሚለውን አምላካዊ ቃል ተግባራዊ በማድረግ በእመቤታችን፣ በቅዱሳን፣ በሰማዕታት፣በመላእክት ስም ጠበል ጸዲቅ አዘጋጅተው ለነዳያን በማብላት እና በማጠጣት ከእመቤታችን፣ ከቅዱሳኑ፣ ከጻድቃኑ በረከት ይሳተፋሉ። የተቸገሩትን መርዳት በእግዚአብሔርም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ትልቅ ዋጋ የሚያሰጥ መሆኑ ይታወቃል።

ምእመኑ ያለውን በማካፈል ከሌለው ላይ እንኳ ቀንሶ በመስጠት የታወቀ ነው። ምግብ፣ ልብስ ገንዘብ የመሳሰሉትን ለሌላቸው ይሰጣል። "ለድሃ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፥ እንደ ስጦታውም መልሶ ይከፍለዋል " ምሳ ፲፱፥፲፯ እንዳለ ጠቢቡ ሀብታም ደሀ ሳይል ለድሆች ይመፀውታል። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ እና ዘርፈ ብዙ ችግር ያለባቸውን ነዳያን ከነሱ የተሻለው የመርዳት ባህል በእጅጉ የተለመደ ነው።

ለዛሬው የትዝብት ጽሑፌ መነሻ የሆነኝ ከመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወደ አራት ኪሎ በሚወስደው መንገድ ላይ ያየሁት እና የሰማሁት አጋጣሚ ነው። መንገዱ የዘወትር መንገዴ ስለሆነ በዚያ ሳልፍ መንገዱ ጠርዝ ላይ ተቀምጠው የሚለምኑ አንድ አዛውንት አያለሁ። ሁሌም ሳያቸው ያሳዝኑኛል ለራሴም "እኚህ አዛውንት በዚህ እድሜአቸው እዚህ ጎዳና ላይ መቀመጥ አልነበረባቸውም፤ ሲሆን ቤታቸው ተቀምጠው በስርዓት ቤተ ክርስቲያን እየተሳለሙ ሥጋ ወደሙን እየተቀበሉ መኖር ነበረባቸው" እላለሁ። ሁሌም ባይሆን አልፎ አልፎ ገንዘብ እሰጣቸዋለሁ። ያን የማደርገው ቢያንስ ምግብ ገዝተው ይበሉበታል ብዬ ስለማስብ ነው።

አንድ ቀን ግን ከዚህ የተለየ ነገር ሲያደርጉ አየኋቸው። አንድ ሰው በፌስታል በፌስታል የተቋጠረ ምግም ይዞ ከዘንቢል እያወጣ በአካባቢው ለነበሩ ነዳያን ያድላል። የራሱን ድርሻ የተቀበለ አንድ ወጣት ድጋሚ ተቀበለና ወደ አዛውንቷ እየሮጠ መጣና "ይኸው አመጣሁልዎት" በማለት እጁን ወደ ርሳቸው ዘረጋ ከአዛውንቷ የተሰጠው መልስ ግን እጅግ አስደንጋጭ ነበረ። "ውሰድልኝ ወደዚያ አሁን በምኔ ልይዘው ነው" ብለው ተቆጡት። ጥሩ ነገር ያደረገ የመሰለው ወጣት በሀፍረት ሽምቅቅ ብሎ ሲመለስ አየሁት።

ከአዛውንቷ የተሰነዘረው ቁጣ ያዘለ መልስ ወጣቱን ብቻ ሳይሆን እኔም አስደነገጠኝ። እኒህ ሴት ገፋፍቶ ጎዳና ላይ ያወጣቸው አንዳች ነገር አለ እሱም ችግራቸው ነው። ሰዎች ከሚቸገሩባቸው ነገሮች ውስጥ በተለይ ጊዜ ከማይሠጡ የሰው ፍላጎቶች ውስጥ አንዱና ዋንኛው ደግሞ ምግብ ነው። በእርግጥ ሰው የተለያየ ችግር ሊኖርበት ይችላል ነገር ግን ሚዛን የሚደፋው የምግብ ችግር ነው። ምግብ የሚገፋ ነዳይ ግን ምን ዓይነት ነዳይ ነው። ሊረዳው የሚፈልገውስ ሰው እንዲህ ዓይነቱን ሰው እንዴት ነው ሊረዳው የሚችለው?

የኒህ አዛውንት ገጠመኝ መነሻ ሆነ እንጂ እንዲህ ዓይነት ትዕይንቶችን በየመንገዱ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ማየት የተለመደ ነው። በተለይ በዓላት በሚከበሩበት ቀን ምእመኑ በእመቤታችን፣ በቅዱሳን ፣ በመላእክት ስም ጠበል ጸዲቅ አድርጎ የሚመጣበት ጊዜ ብዙ ነው። ምግብ ከሆነ ላለመቀበል የሚሸሹ አሊያም ተቀብለው እዚያው ጥለውት የሚሄዱ ነዳያን ጥቂት አይደሉም።

በቀድሞው ዘመን ነዳያን ከረጢት ይዘው መንደር ለመንደር እየዞሩ በመልአኩ ወይም በቅዱሳኑ ስም የሚበላ እና የሚጠጣ ነገር ነበር የሚለምኑት። በምእመን ደጅ ቆመው ስመ እግዚአብሔርን ጠርተው የተሰጣቸውን

በከረጢታቸው ከተው ምእመኑን አመስግነውና መርቀው ነው የሚሄዱት፡፡ አስተውላችሁ ከሆነ እንደነዚህ ዓይነት ነዳያንን መንደር ውስጥ ሲለምኑ ማየት አሁን አሁን ብርቅ እየሆነ ሄዷል ጭራሽ የሉም ማለት ይቀላል፡፡

እውነት ነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የድሆች መጠጊያ ነች እናም ዛሬ ዛሬ በርከት ያሉ ነዳያንን በቤተ ክርስቲያን ደጅ ተኮልኩሎ ማየት የተለመደ ነው፡፡ የሚመጡትም ከመጽዋቹ ደግ ሕዝብ ምጽዋትን ሊቀበሉ ነው፡፡ ሆኖም የተቸገረ ነው ብሎ ምግብ መስጠት ለአንዳንዱ ነዳይ እንደነውር የሚቆጠር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ነዳያንን ማየት ደግሞ ለቸገረው ነዳይ ለመመጽወት እስኪያስቸግር ድረስ ሰውን ጥርጣሬ ውስጥ ይከታል፡፡ ደህነኛውን ከችግረኛው ለመለየት ያስቸግራል፡፡ በእነደዚህ ዓይነቶቹና ከምግብ ይልቅ ትኩረታቸውን በሙሉ ገንዘብ ላይ ባደረጉ ነዳያን ምክንያት ሊመጸወቱ የሚገባቸው ሰዎች ሳይመጸወቱ ይቀራሉ፡፡

እንዲህ ዓይነት ነገር ሲነሳ የሞላ ኑሮ ያላቸው ትርፍ ነገር ፍለጋ አደባባይ የሚወጡ ሀብታም ለማኞችም አሉ፤ ዛሬ ዛሬ መለመን ሱስ ሆኖባቸው እግረ መንገዳቸውን የሚለምኑ ሰዎችንም እያየን ነው፡፡ የውሸት ምክንያት እየደረደሩ የሚለምኑ፣ የውሸት የህክምና ወረቀት ይዘው ለመድኃኒት መግዣ የሚሉ አልፎም በልመና ገንዘብ ጠርቀም አድርገው ወደ ሀገራቸው ለመመለስም ከጎዳና የወጡ አዛውንቶችን ማየት ዘወትራዊ ሆኗል፡፡ ከነዚህ መሀከል የትኛው ነው ትክክለኛ ነዳይ ብሎ ለመመጽወት ሰዎችን እየፈተነ ያለበት ዘመን ነው፡፡

ከነዳያን ጋር ተያይዞ ከዘጠኝ ዓመት በፊት አንድ ወዳጄ ያጫወተችኝን ገጠመኝ እዚህ ላይ ላንሳ፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ የሰሚስተር ወረቀቷን በልመና ግጥም ላይ ለመሥራት ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ አንድ ነዳይ ተቀርብና የልመና ግጥሞች እንዲነግራት እና በመቅረጸ ድምጽ ልትቀዳው ተጠይቀዋለች፡፡ "በአንድ ግጥም ስንት ትከፍዪኛለሽ ?"የሚል ፈጣን ጥቀያቄ ነበር የሰነዘረላት፡፡ ነገሩ የውጤት ጉዳይ በመሆኑ በግጥም ፸ ብር ልትከፍለው ተስማምተው ቤቱ ይቀጥራታል፡፡ በዕለቱ ምግብ አዘጋጅቶ ቡና አስፈልቶ ነበር የጠበቃት፡፡ ይህ አይደለም የገረማት ቤቱ ውስጥ ቴሌቭዥን ሳይቀር ሁሉ ነገር የተሟላ ነው፡፡ በጊዜው መንገድ ላይ የተደረተ ቡትቶ ለብሶ የሚለምነውን ይኸ ነዳይ ከኑሮው ጋር አልገናኝ ብሎአት ተገርማ ነበር ያጫወተችኝ፡፡

የኒህ አአዛውንት ገጠመኝ መነሻ ሆኖ አንዳንድ ገጠመኞችን አልፎ አልፎ አነሳን እንጂ ነዳያን አካባቢ ብዙ ነገሮች ይነሳሉ የዋሁ ምእመን የመጽሐፍ ቅዱሱን "ሁለት ልብስ ያለው ለሌላው ይስጥ፤ ምግብም ያለውም እንዲሁ ያድርግ፡" ሉቃ ፫፥፲፩ የሚለውን ቃል በማሰብ እና ጽድቅን ፍለጋ በግልም በሕብረትም ብዙ ነገር ያደርጋል ሆኖም ለምን ዓይነት ሰው ነው መመጽወት ያለብን የሚል ነው ጥያቄው፡፡

> **እውነት ነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የድሆች መጠጊያ ነች እናም ዛሬ ዛሬ በርከት ያሉ ነዳያንን በቤተ ክርስቲያን ደጅ ተኮልኩሎ ማየት የተለመደ ነው፡፡ የሚመጡትም ከመጽዋቹ ደግ ሕዝብ ምጽዋትን ሊቀበሉ ነው፡፡**

በዚያው መጠን የሚላስ የሚቀመስ ያጡ እየቸገራቸው ኢትዮጵያዊው ባህል ይዞአቸው እጃቸውን ለልመና ለመዘርጋት አፍረው በችግር የሚማቅቁ ብዙ ሰዎች በየቤቱ መኖራቸውን መዘንጋት አይገባም ፤ በንጹህ ልብስ ውስጥ ችግር ያቆራመዳቸው ፤ በእውነት ሊረዱ የሚገባቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ዛሬ ዛሬ የቸገረውን ከደኽነኛው ለመለየት እጅግ አስቸጋሪ ወቅት መሆኑን የምናየው እንዲህ ገሀድ የወጡ ገጠመኞችን ስናይ ነው፡፡ ሆኖም እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ስላሉ በጅምላ በመፈረጅ እጃችንን ከምጽዋት ፤ ልባችንን ከመራራት ልንመልስ አይገባም፡፡

# ''በሃይማኖት መለያየት ምክንያት የምወዳትን ባለቤቴንና ልጆቼን እንዳላጣቸው እፈራለሁ''

***ክፍል ሁለት***

*የተወደደዳችሁ አንባብያ የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ ቀጣዩንና ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ እነሆ፡-*

## ፪. በራስህ እምነት ጠንካራ ሆነህ መገኘት

ክርስቲያን የማያምነውን የትዳር አጋሩን የሚቀድሰው እንዴት ነው? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ክርስቲያን አማኙ በሃይማኖቱና በምግባሩ ከሌሎች እምነት አማኞች ተሸሎ ሲገኝ ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ አንድ ክርስቲያን ሦስት መሰረታዊ ቁም ነገሮች ሊኖሩት ይገባል እነዚህም፡-

**ሀ.** ክርስቲያን የእምነት ጥንካሬ ሊኖረው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮችን ሁሉ እንደሚችልና እንደሚቀይር አምኖ የሚያሰጨንቀውን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ መሆን አለበት፡፡ “በሰው ዘንድ ይህ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል፡፡” (ማቴ. ፲፱፥፳፮) “ቢቻልህ ብለሃል፤ ብታምንስ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል፡፡” (ማር. ፱፥፳፫) “ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ድል ይነሣዋልና፤ ድል መንሣቱም ይህች ናት፤ ዓለምን ድል የሚነሣውም እምነታችሁ ነው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን ድል የሚነሣው ማን ነው?” (፩ ዮሐ. ፭፥፬-፮) ተብሎ እንደተገለጸው፡፡

**ለ.** ክርስቲያን ስለ እምነቱ ማስተማርና መመስከር ይኖርበታል፡፡ አማኙ የማታምን የትዳር አጋሩን ሊቀድሳትና ከዘለዓለም ሞት ሊያድናት ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ ስለ ሃይማኖቱ የሚሰጠው ምስክርነት ነው፡፡ “በሰው ፊት የሚያምንብኝን (የሚመሰክርልኝን) ሁሉ እኔም በእግዚአብሔር መላእክት ፊት አምነዋለሁ፡፡ በሰው ፊት የሚክደኝን ግን እኔም በእግዚአብሔር መላእክት ፊት እክደዋለሁ፡፡” (ሉቃ. ፲፪፥፰-፲) እንዲል፡፡ ክርስቲያን በሃይማኖቱ ሳያፍርና ሳይፈራ በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሚያምነውን የሚመሰክር መሆን ይገባዋል፡፡ በተለይም እንዲህ ዓይነቱ በጋብቻ የመተሳሰር ክሥተት ሲፈጠር አጋጣሚውን ተጠቅሞ በፍቅርና በጥበብ የማያምነውን አጋር ለማዳን እምነትን መመስከር ከአማኙ ይጠበቃል፡፡

**ሐ.** ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን መላበስ ይገባል፡፡ ማንኛውም ክርስቲያን ሃይማኖቱን ከሚገልጽባቸው መንገዶች አንዱ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን መላበስ ነው፡፡ አንዳንድ ሰነፎች ክርስትናን በሕይወት ማሳየት ባለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ከክርስትናው በተቃራኒ ስለሚጓዙ እንኳንስ ኢአማንያንን ሊማርኩ ይቅርና አምላካቸውን የሚያሰድቡ ይሆናሉ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ነው “እነሆ፥ በእናንተ ምክንያት አሕዛብ የእግዚብሔርን ስም ይሰድባሉ፡፡” (ሮሜ ፪፥፳፬) በማለት ነው ያስተማረው፡፡

የክርስቲያን ሕይወት የሚነበብ ወንጌል በመሆን ብዙዎችን ስቦና ማርኮ የሚቀድስ መሆን አለበት፡፡ ክርስቲያን ባል ለማታምን ሚስቱ ፍቅርን፣ ትሕትናን፣ ታዛዥነትን፣ ርኅራኄን፣ ትዕግሥትን፣ ርጋታን፣ . . . ያለማስመሰል

በቋሚነት ካሳያት በሃይማኖቱ መሳቧ አይቀርም። ክርስቲያን አልጫውን ዓለም እንዲያጣፍጥ የተጠራ የእግዚአብሔር መልእክተኛ መኾኑን ማመንና በተግባርም ተልእኮውን መወጣት ይጠበቅበታል። ክርስቲያን ባል የማታምን ሚስቱን አልጫ ሕይወት በቅዱስ ቃሉና በክርስቲያናዊ ሥነ ምግባሩ ለማጣፈጥ እግዚአብሔር የሰጠውን ዕድል መጠቀም ይገባዋል። "ሥነ ምግባራቸው እንዲህ ያማረ ሃይማኖታቸው ምንኛ ቢያምር ይኾን?" እያሉ በክርስቲያኖች ሕይወት ተማርከው ለቅድስና የበቁ ሰዎች እጅግ በጣም ብዙ ናቸው። የእውነተኛ ክርስቲያኖች የጾም፣ የጸሎት፣ የስግደት፣ የምጽዋት፣. . . ክርስቲያናዊ ሕይወት ብዙዎችን ካለማመን ወደ ማመን አምጥቶ በምግባር በሃይማኖት አጽንቶ የመንግሥተ ሰማያት ምርኮኞች አድርጓቸዋል።

ውድ ወንድማችን ባለቤትህን እንደምትወዳት እንገነዘባለን። ክርስቲያን የሆነ ሰው ደግሞ እስከ ሞት ድረስ ደርሶ የሰጠለትን ክርስቶስን እንዲመስል ተጠርቷል። ራስን ከመስጠት የሚበልጥ ስጦታ የለምና እሱ እኛን በመውደዱ ራሱን ነው የሰጠን። እኛም ለምንወደው ሰው የምንሰጠው ስጦታ ለእኛ የምንመኘውንና ውዱን ሀብት ሊኾን ይገባል። ለክርስቲያን የእግዚአብሔር ልጅ ከመኾንና ያዘጋጀለትን ሰማያዊ መንግሥቱን ወርሶ ከመኖር የሚበልጥ ምን ሀብትና ስጦታ ይኖረዋል? እወዳታለሁ፤ እወደዋለሁ፤ ለሚለው ሰው ይህን እንዲያገኝ ካልተመኘና እንዲያገኘውም ማንኛውንም መሥዕዋትነት ካልከፈለላት፥ ካልከፈለችለት እንዴት እወደዋለሁ ሊል/ልትል ይችላል/ትችላለች? የትዳር አጋሩ፣ ልጆቹ፣ ቤተሰቡ፣. . . በጨለማ ውስጥ እየኖሩና ወደ ዘለዓለማዊ ቅጣት እየተጓዙ በግዴለሽነት ማየት ፈጽሞ የሚገባ አይደለም ለዚህም የማይከፍለው ምንም ዓይነት ሰማዕትነት አይኖርም።

ከጻፍክልን ጥያቄ እንደተረዳነው ባለቤትህ ይጠቅመኛል ብላ በያዘችው "እምነቷ" በሥራ ቀድማሃለች። ከልጆችህም አልፎ ተርፎ አንተንም ክርስትናህ ልታወጣህ መንገድ ጀምራለች። በዚህም ምክንያት አብረህ ለመኖር በምታደርገው ግብ ግብ ከውዝፍ ሥራህ ጋራ ተደምሮ የቤት ሥራህን አክብዳብሃለች። ይሁን እንጂ የዘረዘርናቸውን መሠረታዊ ነጥቦች ያለ መነጣጠል ይዘህ ከተነሣህ ጊዜ ሊፈጅብህ ቢችልም ባለቤትህንና ልጆችህን ወደ ሕይወት መመለስህ አይቀርም። መጠንቀቅ የሚገባህ በምንም ዓይነት ሁኔታ ለባለቤትህ ክፉ ወይም ያልተለመደ ደረቅ ቃል እንዳትናገራትና ፊትህንም እንዳታጠቁርባት ነው።

## ፫. በእምነትህ ተስፋ ሳትቆርጥ ለቀጣይ ሕይወታችሁ መፍትሔ ማበጀት

የእግዚአብሔር ቃል "ዘመኑን እየዋጃችሁ ከሃይማኖት ወደ ተለዩ ሰዎች በማስተዋል ሂዱ። ለእያንዳንዱ እንዴት እንደምትመልሱ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን።" ይላል (ቈላስ. ፬፥፭-፮) እንደሚታወቀው ምንም እንኳን ጨለማ በአዳራሹ ውስጥ በአስፈሪነት ሞገሱ ነግሦ ቢኖርም ብርሃን ሲመጣበት ሥፍራውን ለቆ መሸሹ አይቀርም። ጨለማው ቀድሞ ቦታ ይዞ በመቀመጡ ፈርቶና ተስፋ ቆርጦ ሻማውን መለኮስ የሚያቆም የለም። አንተም ምንም እንኳን በቸልተኝነትህ ብትቀደምና ቢረፍድብህም አልመሸም። በቁጭት ከንፈር በመምጠጥ ያለፈውን በማማረር የሚባክን ጊዜ ሳይኾን ጠንክረህ በቁርጠኝነት ከሠራህ ዛሬም ገና ዕድሉና ተስፋው አለህ። ማንንም ሊቀድስ የሚችል፣ በምንም ነገር የማይረክስ፣ እውነት የኾነ፣ በማንኛውም ነገር የማይሸነፍ፣ ጨለማውን ሁሉ የሚገፍ፣ የሰይጣንን ወጥመድ የሚሰባብርና ከኀያሉ እግዚአብሔር ፊት የሚያቆም ሃይማኖት ባለቤት

መሆንህን ማመን አለብህ:: ከነቢዩ ከቅዱስ ዳዊትም ጋር አብረህ፦ “እግዚአብሔር ያበራልኛል፤ ያድነኛልም፤ ምን ያስፈራኛል? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ ምን ያስደነግጠኛል?” (መዝ. ፳፮፥፩) በማለት እየዘመርህ በኀይል ሳይኾን በጥበብ ሚስትህንና ልጆችህን ለመታደግና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመምራት የምትጀምርበት ጊዜ ሩቅ አይኾንም::

እንደዚህ ያለ የትድግና መንፈሳዊ ተግባር ሲፈጸም መረሳት የሌለበት አንዱ ቁም ነገር አልጋ በአልጋ የሆነ መንገድ እንደሌለና ያለ ፈተናም አለመፈጸሙ ነው:: ሰይጣን ዝም ብሎ ስለማያይህ የጠበቅሃቸውንና ያልጠበቅሃቸውን ልዩ ልዩ ፈተናዎች እያመጣ ተስፋ ቆርጠህ እንድትተወው ያለመሰልቸት ይዋጋሃል:: በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደትና በምጽዋት እግዚአብሔርን እየለመንክ፣ ወደ ገዳማት መባዕ በመላክ ገዳማውያን አባቶች በጸሎታቸው እንዲያስቡህ ማድረግና አንተም በጽናት መጋደል ይጠበቅብሃል::

**እንደዚህ ያለ የትድግና መንፈሳዊ ተግባር ሲፈጸም መረሳት የሌለበት አንዱ ቁም ነገር አልጋ በአልጋ የሆነ መንገድ እንደሌለና ያለ ፈተናም አለመፈጸሙ ነው::**

## ፬. ንስሓ አባት በመያዝ በንስሓ መመላለስ

የንስሓ አባት ከሌለህ ከአካባቢህ አጥቢያ የተሻለውን ካህን በማድረግ በካህኑ ምክርና በጸሎቱ ከመጠቀም ጋር የአሸናፊነትን መንፈስና ኀይለ እግዚአብሔርን ለመታጠቅ ትችል ዘንድ ንስሓ ገብተህ ራስህን አንጻ:: በቅርብ የምታገኛቸውን የቤተ ክርስቲያን መምህራን፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የጠነከሩና ሊያግዙህ የሚችሉ የቤተ ዘመድ አባላትንና ጓደኞችህን በአጋርነት መጠቀም ብልህነት ነው:: አቅም በፈቀደ መጠን በፍቅር ሆነህ በጉብኝት ስምም ቢሆን እያግባባህ ወደ ልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት ይዘህ በመሄድ በረከት እንዲቀበሉና የሚያዩትና የሚሰሙትም በልባቸው ጽላት እንዲታተም ዕድል መፍጠር ይገባል::

ከምንም ነገር በፊት ግን አንተ በሃይማኖትህ ጸንተህ መቆም ይጠበቅብሃል:: አሁንም ያ ቆሜአለሁ ብሎ በራሱ የሚታመን ሰው እርሱ እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ::” (፩ ቆሮ. ፲፥፲፪) እንደተባለ የሚቀድመው የአንተ በሃይማኖት ጸንቶ መገኘት ነው:: ለዚህም በቃለ እግዚአብሔር ራስህን መገንባትና በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በምጽዋት እንዲሁም ከላይ በተገለጹት መልካም ምግባራት ሁሉ መጠንከር ይኖርብሃል:: ከእነዚህ ምግባራት ጋራ እግዚአብሔር በጥረትህ ውስጥ እንዲረዳህ በተቻለ መጠን በዕንባ (በለቅሶ) ድንግል ማርያምን በመማጸን ወደ እግዚአብሔር መጮህን አዘውትር:: ለጊዜው ፈተናዎች ተነባብረው ቢያውኩህም በምንም ነገር ተስፋ ሳትቆርጥ ጸንተህ ከታገልክ የኋላ ኋላ ራስህን፣ ባለቤትህን. ልጆችህንና ቤተሰብህን የቅድስና ሕይወት ባለቤት ማድረግህ አይቀርም:: እኛም ሐሳብህንና ፍላጎትህን ለማሳካት የምታደርገው ጥረትህ ለፍሬ ክብር እንዲበቃ ቅዱሳን በጸሎታቸው፥ እመቤታችን በአማላጅነቷ፥ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በቸርነቱ ከአንተ ጋር ሆነው ይረዱህ ዘንድ ፈቃዳቸው እንዲሆን እንመኛለን::